Rift Valley Institute
MAKING LOCAL KNOWLEDGE WORK

Peace Research Facility

# ኃይማኖት፣ ግጭት እና ማኅበራዊ ትስስር፡ ልምዶች ከጅማ ከተማ

በግርማ ደፈረ እና ዮርግ ሃውስቲን

## ማጠቃለያ

- ጅማ ዙሪያዋን በእስልምና እምነት ተከታዮች የተከበበች ብትሆንም፤ በኦሮሚያ ክልል ውስጥ ሰፊ የማኅበረሰብ ስብጥር ያላቸው ነዋሪዎች ከሚገኙባቸው ከተሞች አንዷ ናት። የኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ግንባር (ኢሕአዴግ) መፍረስን ተከትሎ በሌሎች የኢትዮጵያ ከተሞች ኃይማኖትን ብሔር ተኮር አደገኛ ግጭቶች ሲከሰቱ መሰል ግጭቶች ግን በጅማ አልታዩም። ይሁን እንጂ፣ በ1998 እና በ2003 በጅማ ዞን በበሻሻና በአሰንዳቦ አካባቢ በሙስሊም እና በክርስቲያን (ማለትም ኦርቶዶክስና ፕሮቴስታንትን ጨምሮ) እምነት ተከታዮች መካከል ከፍተኛ ግጭት ተከስቶ ነበር።

- በበሻሻ እና በአሰንዳቦ የተከሰቱት ግጭቶች በተለያዩ ኃይማኖቶች መካከል የነበረውን ተቻችሎ የመኖር ልማድን እንዳናጉ ይታመናል። በመሬት ባለቤትነት ላይ ያሉ አለመግባባቶች፣ የተለያዩ የፖለቲካ ዝንባሌዎች እና ከጊዜ ወደ ጊዜ የሚበረታውን አክራሪነት ጨምሮ፤ ለረጅም ጊዜ የቆዩና ያልተፈቱ ጉዳዮች ተደማምረው አዳዲስ ውጥረቶች በተመሳሳይ መልኩ እንዲታዩ አድርጓል። ይህ በእንዲህ እንዳለ ከ2003 ጀምሮ በከተማዋ እና በአቅራቢያዋ ባሉ አካባቢዎች በኃይማኖት መካከል ምንም አይነት የገዘፈ ግጭት ባያጋጥምም፣ የአካባቢው ነዋሪዎች ግን ግጭት ዳግም ሊነሳ ይችላል የሚል ስጋት አላቸው።

- እንደዚህ ዓይነት ስጋት በአንዳንድ አካባቢዎች ጠንካራ የቅድመ ጥንቃቄ እርምጃ ቢያስወስድም፣ በጅማ ግን ሁሉን አቀፍ ውይይት ለማካሄድ እና ሰላሙን ለማስቀጠል በቂ ሥራዎች አልተሰሩም። አንዳንድ የኃይማኖት አባቶች በተለያዩ ማኅበራዊ ጉዳዮች ላይ ቢሳተፉም ቀጣይነት ያለው ድጋፍ ባለማግኘታቸው ብዙ ለውጥ አልመጣም። ከጅማ ኃይማኖት ተቋማት ጉባዔ አጥጋቢ ምላሽ ባለመኖሩም በውይይቶት መዋቅራዊ ጉዳዮችን ሳይፈታ የፖለቲካ ዓላማን ብቻ ያከናውናል የሚል አስተሳሰብ እንዲነሳ አድርጓል።

- ይሁን እንጂ፣ በተለያዩ ኃይማኖቶች ተከታዮች መካከል ያለው ግለሰባዊ ግንኙነት ውስጥ የሚታየው ትስስር እና መተሳሰብ ብርቱ ይመስላል። በከተማዋ በተለያዩ የኃይማኖት ተከታዮች መካከል በሚደረጉ

ጋብቻዎች ላይ አልፎ አልፎ ከሚታዩ ጥርጣሬዎች በስተቀር ኃይማኖታዊ መቻቻል አለ። ጥናቱ በቤተሰብ ግንኙነት፣ በጓደኝነት ወይም በሥራ ቦታ ባሉ የተለያዩ የሕይወት ዘርፎች ውስጥ ከኃይማኖት ልዩነቶች የሚሻገር መከባበር እንዳለ ግኝቱ አሳይቷል። በተጨማሪም፣ እድሮች የተለያዩ ኃይማኖት ተከታዮችን አንድ ላይ በማሰባሰብና ግንኙነቶችን በመፍጠር ረገድ ቅዳሚ መድረኮች ሆነው ተገኝተዋል።

- የጅማ ኃይማኖት ተቋማት ጉባኤ ተደራሽነቱን ለማስፋት እና ተጨማሪ የግጭት ቅድመ መከላከል እርምጃዎችን ተግባራዊ ለማድረግ የገንዘብ ድጋፍ ማግኘት እና መጠናከር አለበት። ከዚህ ጎን ለጎን የመሬትንና የሕዝብ መገልገያ ቦታዎችን ፍትሐዊ ተጠቃሚነትን የሚያረጋግጡ ግልፅ ደንቦችን ማውጣት ያስፈልጋል። በተጨማሪም የመንግሥት ባለሥልጣናት የኃይማኖት ገለልተኝነትን እና የሕግ የበላይነትን በማረጋገጥ ፍትሐዊ የሕዝብ አገልግሎት አሰጣጥን የሚያረጋግጡ ሕገ መንግሥታዊ አሠራሮችን መቀየስ አለባቸው።

## የኢትዮጵያ ሰላም ምርምር ተቋም (Peace Research Facility)

ይህ ሪፖረተ ለኢትዮጵያ የሰላም ምርምር ተቋም (PRF) የተፃፈ ነው። የሰላም ምርምር ተቋም በሰላም እና በግጭት ላይ ወቅታዊ ትንታኔዎችን ከኢትዮጵያውያን ባለሙያዎች ጋር በመተባበር ለግጭት አገናዛቢ ፕሮግራሞች ድጋፍ የሚሰጥ ገለልተኛ ተቋም ነው። ተቋሙ የሚተዳደረው በስምጥ ሸለቆ ጥናት ተቋም (Rift Valley Institute) ሲሆን የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግለት በእንግሊዝ መንግሥት ነው።

*ሪፖረቱ እውቀትን ለሰላም (Knowledge for Peace (K4P)) አካል በሆነው የኢትዮጵያ ጠረፋማ አካባቢዎች መዋዕለ ንዋይ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ፕሮጀክት ሥር የተፃፈ ሲሆን፤ በአሰበ ረጋሳ፣ በደመና አበበ፣ በደረጀ ፈይሳ፣ በአቡበከር ያሲን፣ በጁዌሪያ አሊ፣ በቤኔዲክት ካምስኪ እና በዮሐንስ ይትባረክ በጉዳዩ በተደረጉ አራት ጥናቶች ላይ ያ ጠነጥናል።*

Rift Valley Institute
MAKING LOCAL KNOWLEDGE WORK

Peace Research Facility